ኤርትራዊ ዲሞክራሲያዊ ኪዳን
التحالف الديمقراطي الأرتري

ERITREAN DEMOCRATIC ALLIANCE

Our ref.No. ________________ Date ________________

Your ref.No. ________________

**ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
**የፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር**

ከሁሉ አስቀድሜ በኤርትራዊ ዲሞክራስያዊ ኪዳን ስም የከበረ ሰላምታ ላቀርብሎት እወዳለሁ፡፡

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስተር

ኢትዮጵያ በመስከረም ወር መጀመሪያ 2000ኛ ዓመት የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል ለማክበር በዝግጅት ላይ መገኘትዋ አንዱና ዋነኛ የታሪክ ምዕራፍ ነው፡፡

ይህ በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ ልዩ የማንነት ታሪኳ አንዱ መገለጫዋ የሆነ የሚሊኒየም በዓል ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው የአፍሪካ ህዝቦችም ጭምር ኩራትና ሞገስ የሆነ ታላቅ በዓል ነው፡፡

መላው የኢትዮጵያ ህዝብም ለዚህ በአንድ ሺህ ዓመት አንድ ጊዜ የሚከሰት ይህ ታሪካዊ አጋጣሚ የሚሊኒየም በዓል በከፍተኛ ድምቀትና ዝክር በሚያከብሩበት ወቅት ብሄራዊ ሃገራዊ መግባባትን በማጠናከር በጋራ ራእይ በአንድነት የሚዘምቱበትና የሃገራቸው አወንታዊ ገጽታ ለሌሎች የሚያስተዋውቁበት፡ የተፈጥሮ ጸጋዎችን በጥሩ ሁኔታ እንዲታቀቡ የሚያደርጉበትና የሚያስተዋውቁበት፡ ድህነት ከስሩ የሚነቀልበት፡ በከባድ መስዋእት የተጀመረና የተደረሰበት የሰላምን የዲሞክራሲን ኢኮኖሚያዊ እድገት ጉዞ አበልጽገው የሚገሰግሱባት ዓመት እንዲሆንላቸው ያለን ምኞት ስገልጽ የሚሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም፡፡

ይህ ታሪካዊ በዓል ለመላው የአፍሪካ ህዝቦች ታላቅ ትርጉም ያለው ይሁን እንጂ በተለይ ለሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች ኤርትራና ኢትዮጵያ በታሪክ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በጂኦ ፖለቲካዊ ቅርጸ ምድራዊ አቀማመጥ በቅርብ ጉርብትና የተሳሰሩ ሃገሮች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ፋሽስታዊ የደርግ ስርዓት ለማስወገድ በተደረገው የተራዘመና ጅግንነት የተሞላ አርበኛዊ የትጥቅ ትግል በጋራ የተዋደቁ ጭቁን ህዝቦችም በመሆናቸው ጭምር የተለየ የሚያደርገው መሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡

የሁለቱ ህዝቦች በእኩልነት በጋራ ጥቅምና መከባበር በውስጣዊ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባትና በጋራ ሰላማዊ ኑሮ ላይ የተመሰረተ ዝምድና እንዳይፈጠር ዕንቅፋት የሆነው ጸረ-ህዝብ ዲክታቶሪያዊ የህግደፍ ስርዓት ሳይወገድ በሃገራት ይሁን በዞናችን ይህ ኣቋምና እምነት ባህሪያዊ ቦታውን መያዝ አይችልም፡፡ ኤርትራዊ ዲሞክራስያዊ ኪዳን ከዓላማዎቹ አንዱ ይህንን እውን ለማድረግ ያለማሰላሰል በመታገል ላይ ያለ ሰፊ ሃገራዊ ግንባር ነው፡፡

በመጨረሻ እንኳን 2000ኛ ዓመት የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አደረሳችሁ በማለት በኤርትራዊ ዲሞክራስያዊ ኪዳን ስም ደግሜ የምኞቴን መልእክት እገልጻለሁ፡፡ የ2000 ዓመት ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦችና በኢህወደግ የሚመራው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የደስታና የብልጽግና ዓመት እንዲሆንላቸው እመኛለሁ፡፡

**ከከበረ ሰላምታ ጋር**

**ሑሴን ከሊፋ**
**የኤርትራዊ ዲሞክራስያዊ ኪዳን**
**ፈጻሚ ጽህፈት ቤት ሊቀመንበር**